# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 293 ታህሳስ ፲፩ 2006 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

*የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽብር በመፈጸም ወንጀል ተጠርጥረዉ የቀረቡለትን ግለሰቦች በተከሰሱበት ወንጀል ማስረጃ አላገኘሁባቸዉም ካለ በኋላ ሁሉንም በነጻ አለማሰናበቱ የሚያሳየን የወያኔ ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነጻ አለመሆናቸዉን ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍርድ ቤቶች የገዢዉ ፓርቲ የማጥቂያ መሳሪያዎች መሆናቸዉን ጭምር ነዉ።*

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል ህዝብን የመታደግ እርምጃ መዉሰድ እጀምራለሁ አለ

የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል የተመሰረተበትን አንደኛ አመት ታህሳስ 7 ቀን 2006 ዓመተ ምህረት አከበረ።

ህዝባዊ ሃይሉ የተመሰረተበትን ዓንደኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ባወጣው መግለጫ ያለፈው አንድ አመት

የመሰባሰብ፣ የድርጅት ምስረታ እና መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካና የወታደራዊ ስልጠና የተሰጠበት እንዲሁም የድርጅት ማጠናከሪያና የማጥራት ሂደት የተካሄደበት ጊዜ ነው ብሏል። በስልጠና የመስጠቱ፣ ድርጅት የማጠናከሩና የማጥራቱ ስራ አጥጋቢ ዉጤት መመዝገቡን እና ወደፊትም የሚቀጥል መሆኑን በመጥቀስ በመጪው ዓመት ህዝባዊ ሃይሉ በህዝቦች ላይ የሚደርሰውን ዘርፈ ብዙ ግፍ እና መከራ ለመታደግ እርምጃዎችን መውሰድ የሚጀምርበት መሆኑን አስታውቋል። ህዝባዊ ሃይሉ የአንድ አመት ግዜ በጭንቅና በአሳር ለተያዘች የዛሬይቱ ኢትዮጵያና ህዝቧ እጅግ ረጅም እንደሆነ ህዝባዊ ሃይሉ በሚገባ እንሚገነዘብ እና ባለፈው አንድ አመት ውስጥ የኢትዮጵያን ህዝብ የመከራ፣ የአሳርና የውርደት ህይወት ተባብሶ መቀጠሉን አስታውቋል። በወያኔ ግፈኛ አገዛዝ የተንገፈገፈው የኢትዮጵያ ህዝብ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል የወያኔን አገዛዝ እድሜ የሚያሳጥሩ ፈጣን እርምጃዎችን እንዲወስድ በከፍተኛ ጉጉት እየተጠባበቀ እንደሆነ እና ህዝባዊ ሃይሉን ለመቀላቀል በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ የሃገሪቱ ዜጎች በተጠንቀቅ እንደቆሙም ገልጿል። ህዝባዊ ሃይሉ የሚያደርገው ትግል ታሪካዊ ስህተቶችን ላለመድገም የሚደረግ ትግል መሆኑን በመጠቆም የወያኔ ስርአት ጋር ብቻ ሳይሆን በወያኔ ቦታ የሚተካውን ስርአት ከአድሎና ከዘረኛነት እንዲሁም ከዘረፋና ሃገራዊ ክህደት የጸዳ እንዲሆን እና ዳግም ለኢትዮጵያውያን ውርደትና እንግልት ምክንያት እንዳይሆን ለማድረግ ከራሱ ጋር ሳይቀር የማያቋርጥ ትግል እንደሚያደርግ ጠቁሟል። ህዝባዊ ሃይሉን ለመቀላቀል ለተሰለፉ በሽዎች ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን ትግሉ የሚጠየቀውን የሞራል እና የስብእና ጥብቅነት፣ ከፍተኛ የሃገርና የወገን ፍቅር እና ጥልቅ የሆነ የመስዋእትነት ፈቃደኛነት የሚጠይቅ መሆኑንም አሳስቧል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ አሁንም ሀገር ቆርሶ ለሱዳን ማስረከቡ ከወደ ሱዳን ተሰማ

የንጠኛው መለስ ዜናዊ ሙት መንፈስ ወራሽ የሆነውና የሕወሃት ተላላኪ በመሆን የሚያገለግለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ባለፈው ሰሞን ወደ ሱዳን ካርቱም በማምራት ከሱዳን መንግስት ጋር ለኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን የታጣ መብራት ሃይል ሽያጭ እንደተስማማ ሲነገር የቆየ ቢሆንም ዘግይቶም ቢሆን ዛሬ ከወደ ሱዳን እየተሰማ ያለው ግን በድንበር ማካለልና ስለ ሰላም በሚል ሰበብ የሀገራችንን ድንበር መርቆ አስረክቦ መምጣቱ ነው።

የሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር አረጋገጡት እንደተባለው "ከኢትዮጵያ ጋር የነበረንን የድንበር ይገባናል ውዝግብ በስምምነት ፈተናል" ብለዋል። በዚህ መሰረትም ከሱዳን ጋር በምንዋሰንባቸው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ የድንበር አካባቢዎች ወደ ሱዳን መካለላቸውንና ባካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮችም "ከዚህ በፊት ይህ አካባቢ የከብቶቻችን ማሰማሪያ ነበር አሁን ግን ባካባቢው ለመንቀሳቀስም ማስፈቀድ ይኖርብናል ሲሉ በቁጭት ይናገራሉ።" ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖችም "በሀገራችን ለሕዝብም ሆነ ለሀገር የማይጨነቅ አገዛዝ ነው ያለው። ይህ እኔ ብቻ ልኑር የሆነ አገዛዝም ምንም ነገር ቢሆን ከማስረከብ ወደኋላ የሚል አይደለም። ነገም ለኬኒያና ጂቡቲ ተመሳሳይ የድንበር ልግስና የማይሰጥበት ምክንያት አይታኝም። እኔ አሁን ያሳሰበኝ ማቆሚያው የት ላይ እንደሆነ አለማወቃችን ነው" ይላሉ።

ሌሎች ታዛቢዎችም ዓለማቀፋዊ ሕጎችን በማስታወስ ፋሽስት ወያኔ በሕዝብ የተመረጠ አይደለም። ስለሆነም ወደፊት በሕዝብ የተመረጠና ለሀገርና ለሕዝብ የሚያስብ መንግስት ሲመጣ አላግባብ የተወሰደው መሬታችንም ይመለሳል። ይህን የሀገርን ድንበር የመስለ አንገብጋቢ ጉዳይ ለጊዜያዊ ጠቅምና ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ያስረከቡ የፋሽስት ወያኔ ቁንጮዎችም ቢሆኑ ተጠያቂ መሆናቸው አይቀርም ያላሉ። ከዚህ በፊት ፲600 በ30 ኪሎ ሜትር የሆነውን መሬታችንን ለሱዳን ለማስረከብ በተደረገ ድርድር የበአዴኑ ደመቀ መኮንን ሀገራችንን ለመሸጥ እንደፈረመ ሲዘገብ መቆየቱ ያታወሳል። ይህን በማድረጉም አሁን ላለበት የወያኔ የተላላኪነት የስልጣን ደረጃ ከፍ እንዲል እንደተደረገ አይዘነጋም።

## የጌዲዮ ዞን የሀገር ሽማግሌዎች በረሀብ ተጠቃን የሚል ደብዳቤ ለዞኑ መስተዳድር አቀረቡ

በጌዲዮ ዞን ዉስጥ በተካተቱ ዘጠኝ ወረዳዎች ውስጥ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅና ባልተለመደ መልኩ ከፍተኛ ረሀብ በመከሰቱ የዞኑ የአገር ሽማግሌዎች ህዝቡ ያለበትን አሳሳቢ ሁኔታ በመግለጽ የተፈራረሙበትን ደብዳቤ ከሰሞኑ ለዞኑ መስተዳድር አስገብተዋል። ቀድሞዉንም ቢሆን ረሃብ መግባቱን የሚያዉቁት የዞኑ ባለስልጣኖች የሽማግሌዎቹ መልዕክት አስደንግጧቸዉ መረጃው ይፋ ወጥቶ ተቃዋሚዎች እጅ እንዳይገባ ቀኑን ሙሉ በስብሰባ ተወጥረዉ መዋላቸውን በዞኑ የሚገኙ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የአገር ሽማግሌዎቹ የገጠሩ ህብረተሰብ በከፍተኛ ሁኔታ በመራቡ መንግስት በአስቸኳይ እንዲደርስላቸው ጠይቀዋል። የአገር ሽማግሌዎቹ" የገጠሩ ህዝብ በረሀብ የተነሳ እየፈለሰ ወደ ከተማ እየተሰደደ ነው፣ እናንተ ምን እየሰራችሁ ነው?" የሚል ጥያቄ አንስተዋል።

በዚህ ወር የጌዲዮ ዞን ነዋሪዎች ከፍተኛ ቡና በማምረት የእህል ሽመታ የሚያካሂዱበት ነበር የሚሉት ምንጮች፣ አሁን ግን ሁኔታው ተቀይሮ የህዝቡን ህይወት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የጣለ ረሀብ ተከስቷል ብለዋል። ጌዲዮ ዞን ከ900 ሺ በላይ ህዝብ የሚኖር ሲሆን አብዛኛው ህዝብ ገቢውን የሚያገኘው ከቡና ነው። በመላ አገሪቱ በሚታየው የኑሮ ውድነት ህዝቡ ምሬቱን እየገለጸ ነው። የዞኑን ባለስልጣናት ለማነጋገር ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም። በሌላ ዜና ደግሞ በሸዋ ሮቢት በርካታ መምህራን ስራቸውን እየለቀቁ ነው። መምህራኑ ስራቸውን የሚለቁት ከኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ መሆኑን መምህራን ተናግረዋል። መምህራኑ ወደ ዋና ከተሞችና ወደ ውጭ አገር እየሄዱ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

## ዲያስፖራው አገር ቤት ዉስጥ ከጀመራቸዉ 744 ፕሮጀክቶች ውስጥ ከአራት አንዱ ተግባራዊ አለመሆኑ ተሰማ

ከሚኖሩባቸዉ ከአዉሮፓ፤ ከሰሜን አሜሪካና ከመካከለኛዉ ምስራቅ አካባቢዎች ያፈሩትን ካፒታል ይዘዉ ኢትዮጵያ በመሄድ በንግድ ስራ ላይ ከተሰማሩ ሰዎች ዉስጥ አብዛኛዎቹ በዉሳኔያቸዉ እጅግ በጣም እንደሚጸጸቱ ተናገሩ። ባለኃብቶቹ በግልጽ እንደተናገሩት የወያኔ አገዛዝ ኑና አገራችሁን አልሙ እያለ ይጋብዛል እንጂ አገር ዉስጥ ግን ምንም አይነት ካፒታልን የሚጋብዝ ሁኔታ የለም ብለዋል። እንደ ባለኃብቶቹ አገላለጽ ኢትዮጵያ ዉስጥ ካፒታል ይዞ ሄዶ ንግድ መጀመር ቀርቶ ለጉብኝትም መሄድ እጅግ በጣም ዉጣ ዉረድ አለዉ ብለዋል። በዚህ የተነሳ በዉጭ አገር የሚገኘዉን ቤትና ንብረት ሸጦ አገሬን አለማለሁ ብሎ ኢትዮጵያ የተመለሰዉ ዲያስፖራ ወደ መጣበት እየተመለሰ መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ።

"የዲያስፖራ ተሳትፎ ዓለም አቀፋዊና የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎች" በሚል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዝግጅት ከፍላችን የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2005 ዓ.ም በተወሰኑ ከተማ አስተዳደሮች በተደረገ የዳሰሳ ጥናት በዲያስፖራው ስም ተመዝግበው ለመንቀሳቀስ ካመለከቱት 744 ፕሮጀክቶች መካከል በአሁኑ ሰዓት አገልግሎት ወይም ምርት መስጠት የጀመሩት 120 ፕሮጀክቶች ብቻ ናቸው። ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደስራ ከገቡ ለአንድ ሚልየን 82,972 ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል እንዲሁም ለ2 ሚልየን 131 ሺ 200 ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጥራሉ ብሎ መንግስት ዕቅድ የያዘ ቢሆንም በተግባር ይተረጎማሉ ካላቸዉ ፕሮጀክቶች ዉስጥ ሩቡም በተገባር አለመተግበራቸዉን ለማወቅ ተችሏል።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ጀኔራል የተገኘ መረጃ በግምት ቁጥራቸዉ ከ2-3 ሚሊዮን የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የአለም ክፍሎች ቢኖሩም ለአገራቸው ያላቸው አስተዋጽኦ ግን አነስተኛ ነው ብሎአል። አውሮፓና አሜሪካ የኢትዮጵያውያኑ ዳያስፖራዎች ዋነኛ መዳረሻዎች ሲሆኑ በርካታ የዳያስፖራው አባላትም በእነዚሁ አህጉራት ይገኛሉ ይላል። እውቀና ያገኙ ተመራማሪዎች፤ የጤና ባለሙያዎች፤ የዩንቨርስቲ መምህራን፤ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚሰሩ ባለሙያዎች፤ ድርጅቶችን በመክፈትና በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ኢንቨስትመንት ተቀጣሪዎችም መኖራቸውንም ሰነዱ ያወሳል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ጀኔራል ዲያስፖራው በአገሩ ላይ የሚፈለገውን ሚና ለመጫወት ያልቻለባቸውን መንገዶች ዘርዝሮ አቅርቧል። በቀድሚያ የቀረበው ምክንያት ዲያስፖራው በሀገሪቱ መንግስት ላይ ያለው አመለካከት የተዛባ መሆን የሚለው ይገኝበታል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ከወያኔ ከፋትና እብሪት እንጂ ፍትህ አይጠበቅም

ወያኔ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት የአገራችንን የፍትህ ተቋሞች አንዴ አንደ ቂም መበቀያ ሌላ ግዜ ደግሞ እንደ ማጥቂያ መሳሪያ እየተጠቀመባቸዉ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹንና ጥርስ የነከሰባቸዉን የህብረተሰብ አባላት እያሰረ፤ እያሳደደና እየገደለ ከርሞ ዛሬ ላይ ደርሷል። በተለይ ከግንቦት 1997ቱ ምርጫ በኋላ ወያኔ ብዕርና ወረቀት ይዘዉ በሃሳብና በአመክኖ የታገሉትን ሰላማዊ ዜጎች "ሽብርተኞች"፤ ድምጻችን ይሰማ ብለዉ የመብትና የነጻነት ጥያቄ አንግበዉ በሰላማዊ መንገድ የታገሉትን ኢትዮጵያዉያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ "አክራሪዎች" እያለ ፍርድ ቤት በማቅረብ በፍትህ ተቋሞች በኩል የፖለቲካ ዉሳኔ በማሳለፍ ሠላማዊ ዜጎችን ለረጂም ግዜ እስርና እንግልት ዳርጓል።

ወያኔ ለኢትዮጵያና ለዜጎቿ ደንታ የሌለዉ እና ከስህተቱ የማይማር የግብዞችና የዘረኞች ስብስብ ስለሆነ አሁንም የአገሪቱን የፍትህ ተቋሞች እንደ ማጥቂያ መሳሪያ እየተጠቀመ የኢትዮጵያን ህዝብ በፍርሃት ጨለማ ዉስጥ ሸብቦ እየገዛ ለመኖር የቆረጠ ይመስላል። ባለፈዉ ሳምንት አጋማሽ ላይ የወያኔ አገዛዝ ከአንድ አመት ተኩል በላይ እስር ቤት ዉስጥ አጉሮ ያቆያቸዉን የድምጻችን ይሰማ መሪዎች ከፊሎቹን በነፃ ተለቅቀዋል የሚል ከፊሎቹን ደግሞ ተከላከሉ የሚል ትርጉም የለሽ ብይን ሰጥቷል። በህወሀት ታጋዮች የተሞላዉ ፍርደ ገምድሉ የወያኔ ፍርድ ቤት እንኳን ተከሳሾቹ በተከሰሱበት ሽብር የመፈጸም ወንጀል ምንም አይነት ማስረጃ አልተገኘባቸዉም ሲል አገዛዙ ግን የፖለቲካ ክንዱን በመጠቀም ማስረጃ ያልተገኘባቸዉን ሠላማዊ ዜጎች የተከሰሱበትን መሰረተ ቢስ ክስ ተከላከሉ የሚል የፖለቲካ ዉሳኔ ሰጥቷል።

የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሙን ህብረተሰብ የመፍትሄ አፈላላጊ ቡድን መሪዎች ፍርድ ቤት ያቀረባቸዉ ለምዕራባዉያን ለጋሾቹና ለአለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍትህ ያለ ለማስመሰል ነዉ እንጂ ወያኔ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን የፈረደባቸዉ ያሰራቸዉ ቀን ነዉ። የወያኔ የፍትህ ታሪክ በግልጽ እንደሚያሳየን ወያኔ ግለሰቦችን የሚያስረዉ ለክስ የሚያበቃ ማስረጃ አግኝቶባቸዉ አይደለም፤ ይልቁንም ወያኔ ማስረጃዎችን እየፈበረከ ለፍረድ ቤቶች የሚያቀርበዉ ግለሰቦችን ካሰረና ሰብዓዊ መብታቸዉን ከገፈፈ በኋላ ነዉ። ለምሳሌ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን አስሮ ብዙም ሳይቆይ የእነዚህን ሰላማዊ ዜጎች ተክለ ሰዉነት ጥላሸት የቀባና ግለሰቦቹን ያለ ማስረጃ ወንጀለኛ አድርጎ የፈረጀዉን "ጂሐዳዊ ሀረካት" የሚል የፈጠራ ድራማ ሰርቶ ለህዝብ አቅርቧል።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽብር በመፈጸም ወንጀል ተጠርጥረዉ የቀረቡለትን ግለሰቦች በተከሰሱበት ወንጀል ማስረጃ አላገኘሁባቸዉም ካለ በኋላ ሁሉንም በነጻ አለማሰናበቱ የሚያሳየን የወያኔ ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነጻ አለመሆናቸዉን ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍርድ ቤቶች የገዢዉ ፓርቲ የማጥቂያ መሳሪያዎች መሆናቸዉን ጭምር ነዉ። የወያኔን አገዛዝ ከሌሎች አምባገነኖች ለይቶ አደገኛ የሚያደርገዉና በምዕራባዉያን መንግስታትና በቀላጤዎቻቸዉ እንዲወደስ ያደረገዉም ይሄዉ አገዛዙ የሚቃወሙትን ኃይሎች የሚያጠፋቸዉ እንደሌሎቹ አምባገነኖች በግልጽ ሳይሆን በህግ ሽፋን ዉስጥ በስዉር መሆኑ ነዉ።

የወያኔዉ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ወንጀል ተከስሰዉ የቀረቡለትን ነገር ግን ምንም መረጃ ያላገኘባቸዉን የድምጻችን ይሰማ መሪዎች ገሚሶቹን በነፃ ለቅቆ የተቀሩትን ጥፋተኛ አለመሆናችሁን አረጋግጡ ብሎ መወሰኑ የወያኔን ሁለት እኩይ አላማዎች ያሳየናል። የመጀመሪያዉ የወያኔ አላማ በአላማቸዉ ጸንተዉ የቆሙትን የድምጻችን ይሰማ መሪዎች መከፋፈል ሲሆን፤ ሁለተኛ አላማዉ ደግሞ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸዉን የክስ መዝገቦች በሚገባ አጣርተዉ ዉሳኔ የሚሰጡ መሆናቸዉን ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ለማሳየት ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ግን እንደዚህ አይነቶቹን የወያኔ እኩይ ተግባሮች ካወቀ ዉሎ አድሯል፤ ስለሆነም ከወያኔ ፍትህ ጠብቆ አያዉቅም፤ ወያኔ የክፋትና የበቀል ምንጭ ነዉና ለደፊትም አይጠብቅም። የድምጻችን ይሰማ መሪዎችም ሆኑ ከእነሱ በፊት በግፍ ታስረዉ መከራቸዉን የሚያዩት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፤ ጋዜጠኞችና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች የታሰሩት ለቆሙለት የፍትህ፤ የነጻነትና የእኩልነት አላማ እንደ አለት ጸንተዉ በመቆማቸዉ ነዉ። እነዚህ ጀግኖች የታሰሩለት አላማ የሁላችንም አላማ ነዉና ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት የጠማን ኢትዮጵያዉያን ክንዳችንን አስተባብረን የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ በሆነዉ በወያኔ ስርዐት ላይ ክንዳችንን በጋራ እናንሳ!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## ዲያስፖራው አገር ቤት ውስጥ ከጀመራቸዉ 744 ፕሮጀክቶች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዲያስፖራው በአሁኑ ሰዓት ኢህአዴግን ከመደገፍ ይልቅ በኤርትራ ለሚንቀሳቀሱ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ቡድኖች መደገፍ ይፈልጋል የሚለው ሰነዱ፤ ከመንግስትም ወይም ከተቃዋሚዎች ከመጎዳኘት ይልቅ መሃል ሰፋሪ መሆን የሚመርጡ የዲያስፖራ አባላት መኖራቸውን ይገልጻል። በክልሎች ያለው የመልካም አሰተዳደር ችግር፤ ሙስና፤ ዲፕሎማቶች ተገቢውን ስራ አለማከናወናቸው በመንግስት በኩል የሚታዩ ድክመቶች ናቸው በማለት የሚጠቅሰው ሰነዱ፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ በሚመጡ የዲያስፖራው አባላት የሚታዩ ችግሮች በማለት ከዘረዘሩዋቸው መካከል ደግሞ" በተሠጣቸው የኢንቨስትመንት ቦታ ላይ ለማልማት ያላቸው አቅም አናሳ መሆን፣ የተቀበሉትን ቦታ ለሌላ አካል ለማስተላለፍ መሞከር፤ ፈጥኖ ወደ ስራ አለመግባትና አጥሮ ማስቀመጥ፣ የመሬት ሀብት ስለሚባክን ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቅሬታ መነሳት፤ እነሱ በሚፈልጉበት ጊዜና መንገድ ጉዳያቸው ካልተፈፀመ መንግስትን የማማረርና የመልካም አስተዳደር ችግር እንደሆነ የማስመሰል ሁኔታዎች መኖር፣ ከዳያስፖራዎቹ ከራሳቸው ምን እንደሚጠበቅና የኢንቨስትመንት አሠራር ህግን ያለማወቅ፤ ለጠየቁት ፕሮጀክቶች መሬት ማግኘታቸውን ሳያረጋግጡ ለፕሮጀክቶቻቸው አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎችን ግዥ ፈጽመው በወደብ የመጋዘን ኪራይ ያለአግባብ ወጭ እያወጣን ነው ብለው ማማረር፤ አብዛኛው ዳያስፖራ ወደ ክልሉ መጥቶ ለማልማት ሲፈልግ ቅድሚያ መረጃ የሚሰበስበው በየግለሰቡ መሆኑ" የሚሉት ይገኙበታል።

በአገር ውስጥ ያሉት የዳያስፖራ ተወካዮች ጉዳይ ለማስፈጸም ችግር ካጋጠማቸው ውጭ ለሚኖሩት ዳያስፖራዎች ችግሩን አጋኖ የመናገር ሁኔታ መኖር፤ በተወካዮቻቸው ድክመት ፕሮጀከቶቻቸው በሚፈልጉት መንገድ ካልተፈጸሙላቸው መንግስትን የማማረር ሁኔታ መኖር፣ በክልሉ የተመዘገበውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ለውጥ አምኖ ለመቀበል ያላቸው ዝግጁነት አናሳ መሆን፤ ዳያስፖራው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካወጣ በኋላ ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር እንዲገባ ለማድረግ የሚሰጠው ድጋፍና የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆን፤ ዳያስፖራው ለሚያቀርበው ጥያቄ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ በመረጃና በአሰራር ላይ ተመስርቶ በወቅቱ ምላሽ ከመስጠት ይልቅነገ ዛሬ በማለት ስለሚያጉላላና ለአላስፈላጊ ወጭ ስለሚዳረግ መንግስትን ከማማረራቸውም በላይ ሌሎች ዳያስፖራዎችን ወደ በሀገራችን መጥተው በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑ በሰነዱ ላይ ተዘርዝሮ ቀርቧል።

"ከፍተኛ አመራሮች ወደ ውጭ አገራት ሂደው ዳያስፖራውን ወደ ሀገሩ መጥቶ በተለያዩ ኢንቨስትመንቶች እንዲሳተፍና ሀገሩን እንዲደግፍ ሲያወያዩት 'ኑና አልሙ ትላላችሁ ወደ ክልላችን ስንሄድ ግን እንጉላላለን፤ ተገቢውን አገልግሎት አናገኝም፤ የተሻሉ ሰዎችም ተስፋ ቆርጠውና ክልላቸውን ጠልተው ሲመለሱ እናያለን…' በማለት እንደሚናገሩ ሰነዱ ይገልጻል። ሰነዱ በትግራይ 95፣ በአማራ 120፣ በአፋር 60፣ በቤንሻንጉል 51፣ በኦሮምያ 114፣ በሀረሪ 96፣ በሶማሊ 83፣ በደቡብ 111 እንዲሁም በጋምቤላ 33 የዲያስፖራ ፕሮጀክቶች መመዝገባቸውን ያሳያል። ከህዝብ ብዛት አንጻር ሲነጻጸር በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ክልሎች የዲያስፖራው ተሳትፎ እጅግ አነስተኛ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በሚኖርባቸው በእነዚህ ክልሎች የመጣው ዲያስፖራ ተሳትፎ አነስተኛ መሆን ከፖለቲካው ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆን እና አለመሆኑ በሰነዱ ውስጥ አልተገለጸም።

---

## የግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል ህዝብን የመታደግ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ህዝባዊ ኃይሉ በተደጋጋሚ ለምን እርምጃ ወስዳችሁ መኖራችሁን አታሳዩም እየተባለ የሚጠየቀዉን ጥያቄ ሲመልስ ህዝባዊ ሀይሉ "ለተራ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ስንል በቂ ዝግጅት ያልተደረገበት የሃገሪቱን ውድ ልጆች በከንቱ የሚማግድ ጀብደኛ እንቅስቃሴ አናደርግም። በውሸት ተስፋ ህዝብን አንመግብም። አይናችንን ከዋናው የኢትዮጵያና የህዝቧ ጠላት ከሆነው ከወያኔ ላይ አንስተን በሌሎች ወያኔን እቃወማለሁ በሚሉ ሃይሎች ላይ አንተክልም። ከወያኔ ሌላ ወደ ጎን የምንዋጋው፣ የምንጨቃጨው አታካራ የምንገጥመው ምንም ሃይል አይኖርም። ወያኔን ለመምታት ህዝባዊ ሃይሉ የጨበጠው ቡጢ ወገኖቻችን በፍቅር ለመጨበጥ የሚዘረጉ ጣቶች እንዳሉት በጸረ ወያኔ ዴሞክራሲያዊ ትግሉ ከልባቸው ለመተባበር ለሚፈልጉ ሃይሎች ሁሉ ግልጽ እናደርጋለን።" ሲል አትቷል።በግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል አመራሮች ላይ መንግስት የመግደል ሙከራ ማድረጉና መክሸፉ ይታወሳል። በቅርቡ ደግሞ ከአመራሩ ጋር ለመደራደር ጥያቄ ማቅረቡና ንቅናቄው ውድቅ ማድረጉ ይታወቃል።

---

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሠራዊቱ ሆይ እንድታደምጠን እንፈልጋለን !!!

በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል  ድህረ ገፅ ላይ የሠራዊቱ ዋና እሴቶች ተብለው አራት ነገሮች ተዘርዝረዋል።

**1ኛ. ከራስ በፊት ለህዝብና ለሃገር**
**2ኛ. ክሙስና የፀዳ እና ሙስናን የማይሸከም**
**3ኛ. ያልተሸራረፈ ዲሞክራቲክ አስተሳሰብ**
**4ኛ. በማንኛውም ግዳጅ/ሁኔታ የላቀ ውጤት ናቸው**

እነዚህን እሴቶች ያየ ሌላ ሰው በእነዚህ መሠረቶች ላይ የቆመ ሠራዊት እያለ እንደምን ሁኖ ይሄ ሁሉ ግፍ በዚያች አገር ሊፈፀም ቻለ ብሎ መጠየቁ አይቀርም።ጥያቄው አግባብነት አለው። በእነዚህ መሠረቶች ላይ የቆመ ሠራዊት እያለ እንደምን ሁኖ ነው ህዝብ የሚያልቀሰው? እንደምንስ ሁኖ ነው ህዝቡ በመረጠው መሪ መመራት ያልቻለው ? እንደምን ቢሆን ነው የሠራዊቱ አዛዦች የሙስና ጥሩ ምሳሌ እና መልክ ሆነው ሊጠቀሱ የበቁት? ምንስ ቢሆን ነው "ሙስና ምን ይመስላል ቢሉ "የኢታማዦር ሹሙን ሳሞራ የኑስን ይመስላል" እስከ ሚባል ድረስ የተኬደው?

ስማን አንተ የሠራዊቱ አባል ! አንተ የህዝብ ልጅ ነህ። የወጣኸው ከህዝብ አብራክ፤ ነገም ተመልሰህ የምትገባው እዚያው ወደ ወጣኸበት ህዝብ ነው። ዞሮ መግቢያህ የሆነው ህዝብህ ግን የመከራው ዓይነትና ብዛት ፅዋውን ሞልቶ በመፍሰሱ ወገንህ ቤቱን ዘግቶ እያለቀሰ ነው። ከጎነህ የህዝቡን ደህንነት እንጠብቃለን ብለው የተሠማሩት የመንግስት ደህንነት ሠራተኞች ወገንህን የሚያዋርዱ ሁነዋል። ባለፈው ሰሞን እነዚሁ የመንግስት የደህንነት ሠራተኞች በአቶ አበበ አካሉ ላይ "ጀሮ ጭው የሚያደርግ ነውር ነገር መፈፀማቸው ተሰምቷል"። አቶ አበበ  አካሉ የፖለቲካ ድርጅት መሪ እና አስተማሪ ናቸው። የደህንነት ሠራተኞች ነን በሚሉ ቡድኖች ተይዘው በልዩ ልዩ ማሰቃያ መንገዶች ተጠቅመው የሚያሰክር መጠጥ እንዲጠጡ አደረጓቸው። ከዚህ በኋላ የሆኑትን ሲገልጹ "በወንድ ልጅ ላይ ሊፈፀም የማይገባ፤ በአገራችንም ነውር የሆነ ነገር ፈፀሙብኝ" ብለዋል። እንግዲህ ይሄን ነውር ነገር ነው ***"ጆሮ ጭው"*** የሚያደርግ ብለን ለመግለጽ የፈለግነው። እንግዲህ አንተን ጋሻና መከታ አድርጎ የቆመው ህወሃት የሚመራው መንግስት እንዲህ ዓይነቱን ጆሮን ጭው የሚያደርግ ነውር ሲፈፀም ሰምተህ ዝም ማለትህ ለምን ይሆ? አንተ እያለህ እንደምን ሁኖ በኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት ያሠማራቸው ቡድኖች የፖለቲካ ድርጅት መሪ እና መምህርን ይዘው ነውር ነገር እንዲፈፀምበት ያደርጋሉ? ከራስ በፊት ለህዝብና ለአገር እቆማለሁ ብለህ ስታበቃ ይህን የመሰለ ግፉ በአገርህ ሲፈፀም እያየህ ዝም ትላለህ። ይሄ ማለት ምንድ ነው?  የአንተ ለህገ መንግስቱ ታማኝነት ከወዴት አለ? አንድ ዜጋ ህገ መንግስታዊ መብቱ ሲገፈፍ እያየህ ዝም ካልክ ነገ እንዲህ ያለ ወንጀል ባንተ ላይ ሲፈፀም የሚከላከልልህ ህግ እንደሌለ አታውቅምን? የአንተ ታማኝነት ለህገ መንግስቱ መሆን ሲገባው አንተ ግን ህገ መንግስቱን ትተህ የህወሃት አገልጋይ መሆንን መርጠሃል። ይሄ ደግሞ አገርህንም ህዝብህንም እንድትበድል አድርጎሃል። በዚህም ከህዝብህ እና ከወገንህ ጋር ቅራኔ ውስጥ ትገባለህ። ነገ ብትወድቅ የሚያነሳህ፤ ብትታመም የሚጠይቅህን ታጣለህ። ይሄ ደግሞ ላንተ ጉዳት እንጂ ጥቅም አይደለም።

አንተ የሠራዊቱ አባል የሆነከው ወገኖችህን የማያውቁ ጥቂቶች ከላይ ሁነው፤ አንተ ደግሞ ከታች እንርሱን ተሸክመህ የወገኖችህን መከራ አብዝተህ ለመኖር አልነበረም። ትግሬን ነፃ እናወጣለን ብለው ራሳቸውን የሾሙ ጥቂት ቡድኖች የአገሪቷን ስልጣን ከተቆጣጠሩ ዘመን ጀምሮ መከላከያ ኃይሉ ለህዝቡ ጋሻ መከታ መሆን ሲገባው የገዛ ህዝቡን ደም በከንቱ በየቦታው የሚያፈስ ሁኗል። የገዛ ወገንህ ከቀየውና እትብቱ ከተቀበረበት ሥፍራ ተፈናቅሎ የትም ሲጣል አንተ የሠራዊቱ አባል የዚህ ግፍ አስፈፃሚ እንድትሆን ሁነሃል። አንተ የአገር መከላከያ ሃይል ከማንም በላይ ከህዝቡ ጎን መቆም ሲገባህ ልትቆምለት የሚገባውን ህዝብ ትተህ የጥቂት የጨለማው ቡድኖች ፍላጎት አስፈፃሚ አካል እንድትሆን ተደርገሃል። አዲስ አበባ ላይ ግደል ስትባል ህፃናትን ሳይቀር ትገድላለህ። አጋዴን ወርደህ የዘር ማጥፋት ወንጀል ትፈፅማለህ። ጋምቤላ ላይ ያገኘኸውን ሁሉ ታጠፋለህ፤ የእርሻ መሬታቸው ተቀምቶ ለባእድ ሲሰጥ አንተ ዋና አስፈጻሚ ሆነህ ትሠራለህ። ይሄ ወንጀል ነው።ይህን ወንጀል ታዝዤ ፈፅሜያለሁ እያልክ ከደሙ ነፃ ለመሆን ትውተረተራለህ። ታዞ ሰው መግደል ታዛዥነት ሳይሆን ቅጥረኛ ነፈሰ ገዳይነት ነው። አዛዦችህ የህዝብ ጠላቶች ስለሆኑ ህዝቡን ለማዋረድ የሚፈጽሙትን ወንጀል በአንተ አማካኝነት ሲያስፈፅሙ አይሆንም ማለት ስትችል የወንጀለኞች መሣሪያ መሆንን መምረጥህ በምንም መንገድ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት መሆኑን ልናስታውስህ እንወዳለን። አዛዦችህ ገበሬውን ከይዞታቸው አፈናቅለው ሜዳ ላይ ጥለው መሬቱንም ለባእድ ሸጠው ብሩን ተከፋፍለው በውጪ አገራት ባንክ ያጠራቅሙታል።አንተ የወገኖችህን ደም በከንቱ አፍስሀ ቂም በቀል ታከማቻለህ። የህዝብህን ከበሬታ እና ፍቅር ታጣለህ። በእርጅናህና ጉልበትህ በደከመ ዘመን ጠያቂ እንድታጣ ትሆናለህ። ያኔ ጉልበትህ በዛለ፤ ኃይልህ በደከም ዘመን የሰፈሩ ሰው የዚያ የህወሃት አገልጋይ ነበር ህወሃት መጥቶ ይጠይቀው እያሉ ይዘባበቱብሃል። የድሃ ሃብት ዘርፎ ባንክ ቤት የከፈተውን የሳሞራ የኑስን ድምፅ ለመሥማት መምረጥህ የሚያተርፍልህ ይሄን ነውና ለራስህ ስትል የህዝብህን የሲቃ ድምፅ ትሰማ ዘንድ እንመክርሃለን።

አንተ የሠራዊቱ አባል ከመልካም ህዝብ አብራክ የወጣኽ ሃይማኖት ያለህ እንደሆንክ እናውቃለን። ያሳደገህ ማህበረሰብ እና ሃይማኖትህ ነፍሰ ገዳይ አድርጎ አላሳደገህም። አንተም ወደ ሠራዊቱ ስትገባ እንደ ቃየል የወንድምህን ደም በከንቱ ልታፈስ እና ዘረኞችንና ሌቦችን ተሸክመህ ልትኖር አልነበረም። ወደ መከለካያ ኃይሉ የተቀላቀልከው አገርህን ለመጠበቅ፤ ለህዝብህ ጋሻና መከታ ለመሆን ነበር። ይሄ ግን እየሆነ አይደለም። በእውቀትም ይሁን ባለማወቅ አዛዦችህ የወገንህን ደም በከንቱ እንድታፈሰ አድርገው ሲያበቁ እነርሱ ከድሃው ወገንህ ጉሮሮ ላይ በነጠቁት ገንዘብ ውስኪ ይራጫሉ። በአሜሪካና በአውሮፓ የሚኖሩ ታላላቅ ሙዚቀኞችና የሲኒማ ተዋናዮች የሚኖሩትን የሚመስል ኑሮ ይኖራሉ። አንተ የሠራዊቱ አባል ግን ካሊስ ለመቀየር ትቸገራለህ፤ እጆችህን የሚያዩ ዘመዶችህን ለችግራቸው ልትደርስላቸው ባለመቻለህ ዘወትር በሰቀቀን ትኖራለህ። ጄኔራል ተብየዎች ለቤታቸው ማስጌጫና ማሞቂያ ከውጪ አገር በትዕዛዝ እያስመጡ የተቀናጣ ኑሮ ይኖራሉ። ልጆቻቸውንም በውጪ አገራት ዩንቨርሲቲዎች ልከው ያስተምራሉ። በአጭሩ ኢትዮጵያ ለእነርሱ ምድረ ገነት ስትሆን ለአንተና ለወገኖችህ ግን የምድር ሲዖል ሁናለች። የመከላከያ ሃይሉ ከሙስና የፀዳ፤ሙስናንም ተሸክሞ መኖር አይገባውም ቢባልም አንተን ከላይ ሁነው የሚያዙህ ዋና የሙስና ምሳሌዎች ሁነው የሚጠቀሱ ናቸው። ለምሳሌ ኢታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ አገሪቷን ከሚዘርፉ ዋና ዋና ሌቦች መካከል ቀንደኛው  ሲሆን ዘርፎ ባከማቸው ገንዘብ የባንክ ቤት ባለቤት ለመሆን በቅቷል። ሌላው ዋና ሌባ ደግሞ ከሰሞኑ በሌተናል ጄኔራል ማዕረግ የተሾመው ዮሃንስ ገ/መስቀል ሲሆን እርሱም በድርሻው በመቶ ሚሊዮን ብር በሚቆጠር ገንዘብ ህንፃ አስገንብቶ በየወሩ ከአስር ሺህ ዶላር በላይ ያገኛል። አዛዦችህ ሚሊየነሮች ሁነዋል። የእነርሱ ሃብትና የደስታቸው ምንጭ ከአንተና ከወገኖችህ ጉሮሮ የተነጠቀ ገንዘብ መሆኑን ልታውቅ ይገባሃል። ለናሙና ያክል እነዚህን ሁለት ሌቦችን ብቻ ጠቀስንልህ እንጂ ካርታ ይዘው የቆሙበትን ሥፍራ እንኳ መለየት የማይችሉ ጄኔራል ተብለው የተሾሙ በሙሉ ቀንደኛ ሌቦች  ናቸው።

አንተ የህዝብ ልጅ የሠራዊቱ አባል እንዲህ ዓይነት ሌቦችን ተሸክመህ እንድትኖር የሚያደርግህ ምንድ ነው ?

ይሄውልህ አንተ የሠራዊቱ አባል በወገኖችህ የተወደድክና የተከበርክ እንድትሆን፤እነዚህ ሌቦችም ከጫንቃህ ላይ ወርደው ዜጎች ሁሉ ከፍርሃት ተላቀው በእኩልነት እንዲኖሩ መታገል አለብህ። በወደክ ግዜ የሚያነሳህ፤ ብትታመም የሚጠይቅህ፤ ብትራብ እጁን የሚዘረጋልህ፤ ብትጠማ የሚያጠጣህ ህዝብ እንጂ ህወሃት አለመሆኑን ነግረንሃል። ህወሃትማ አንተን በሶማሌ፤ በሱዳን እና በኦጋዴን አሰማርቶ በአንተ ደምና አጥንት ነግዶ ትርፉን እርሱ ይጫወትበታል እንጂ አንተ የትም ብትወድቅ የህወሃት ችግር አይደለም። አንተ የሠራዊቱ አባል ግን ለራስህ እውቅበት። ህወሃትን የሚታገለው ኃይል ብዙ ነው። ህወሃት የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ ድርጅት ነው። ከህዝብ ጠላት ከሆነ ቡድን ራስህን በቶሎ ለይ።ወንድሞችህ እና እህቶችህ ለፍትህ፤ ለነፃነት እንዲሁም ለእኩልነት ሲሉ ብረት አንስተዋል።የህዝብ ጠላት የሆነውን ህወሃትን በሚገባው ቋንቋ ለማናገር እየተፋጠኑ ነው። አንተ የሠራዊቱ አባል ለዘረኛው ለሳሞራ የኑስ የምትሞትለት ለምንድ ነው? ሳሞራ በወገኖችህ ላይ እንድትዘምት የሚያደርግህ ከህዝብ ዘርፎ የከፈተውን ባንክ በስተርጅናው ቁጭ ብሎ ሊበላ እንጂ ለህዝብ አስቦ አይደለም። ዮሃንስ ገ/መስቀልም ተነስና ወገኖችህን ውጋ ሲልህ በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረቱን ከየት እንዳመጣው እንዳይጠይቅ እንጂ ለአንተ ነፃ መውጣት እንዳልሆነ ልትገነዘብ ይገባሃል።

በመጨረሻም አንተ የህዝብ ልጅ ሆይ!!! ሳሞራንና ዮሃንስን የመሰሉ በሙስና የተጨማለቁትን ተሸክመህ መኖርን መምረጥ የለብህም። እነዚህ እኛ ከሌለን አገሪቷን እንበትናታለን እያሉ የሚያናፉ ትዕቢተኞችን "እኔ እያለሁ አገሬ አትፈርስም፤ ህዝቤም አይበተንም" ማለት መጀመር አለብህ። እኛም ከጎንህ አለን። ብትወድቅ ልናነሳህ፤ ብትቆስል ቁስልህን ልናክምልህ፤ ብትሰዋ በሶማሌ ጎዳናዎች ላይ አስከሬኑ እንደተጎተተው ወንድምህ ተረስተህ እንዳትቀር ታሪክህን ፅፈን ለትውልድ ልናስተላልፍልህ በየቦታው ቆመናል። አትፍራ ! ወገንተኛነትህ ከህዝብ ጋር ይሁን እንጂ የህዝብ ጠላት መሆንን ከመረጡ ህወሃቶች ጋር እንዳይሆን አጥብቀን እንመክርሃለን። እምቢ ብለህ ከባንክ ባለቤቱ ከሳሞራ የኑስ፤ እንዲሁም ከሚሊየነሩ ከዮሃንስ ገ/መስቀል ጋር መቆምን ከመረጥክ ግን ዛሬ የተመርኮዝከው ብረት ነገ የሸንበቆ ምርኩዝ እንደሚሆን ልናስታውስህ እንወዳለን። የሸንበቆ ምርኩዝ ይሰበራል፤ ሲሰበር ደግሞ ተመልሶ ይወጋልና የሚበጅህን ምረጥ። ከህዝብና እና ሳሞራ የኑስን ከመሰሉ ምናምንቴ ሌቦች አንዱን እንድትመርጥ ልንመክርህ እንወዳለን። እኛ አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ወያኔ/ኢህአዴግ ቴዎድሮስ አድሐኖምን መገሰጹ ተሰማ

ዘረኞቹ የህወሀት መሪዎች በመጪዉ ምርጫ የጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታ እንዲረከብ እያዘጋጁት ነዉ ተብሎ የሚነገርለት ዶ/ር ቴዎድሮስ አድህኖም “በሳውድ አረቢያ ላይ ተመጣጣኝ የአጸፋ እርምጃ እንወስዳለን” ብሎ በመናገሩ ከፍተኛ ወቀሳና ሂስ እያቀረረቡበት መሆኑን ዘጋቢዎቻችን ለጉዳዩ ቅርበት ያለቸዉን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። የወያኔ/ኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር አስቸኳይ ስብሰባ የጠሩ ሲሆን ዶ/ር ቴዎድሮስም ያለግንባሩ ውሳኔ እንዲህ አይነት ጠንካራ አስተያየት ለምን እንደሰጠ እንዲያብራራ ተጠይቋል። ዶ/ር ቴዎድሮስ በጉዳዩ ላይ በቂ ማብራሪያ ለመስጠት ባለመቻሉ ግለ-ሂሱን እንዲዉጥ ከመጠየቁ ባሻጋር ከፓርቲው ይልቅ የግል ዝናህን እየገነባህ ነዉ የሚል ትችትም ቀርቦበታል።

የሳውድ አረቢያ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒሰትር ቴዎድሮስ አድህኖም በሰጠዉ መግለጫ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጠው ለ አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ ደብዳቤ ማስገባቱን ተከትሎ ነው ግምገማው የተካሄደው። በሳውድ አረቢያ መንግስት ደብዳቤ የተደናገጡት አቶ ሀይለማርያም ወዲያውኑ በቴሌቪዥን ቀርበው ከሳውድ አረቢያ ጋር የቆየ የዲፐሎማሲ ግንኙነት መኖሩን፣ ይህን ግንኙነት አሁን በተፈጠረው ችግር እንደማይለወጥና ለወደፊቱም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።አቶ ሀይለማርያም የተናገሩትን ተከትሎ በሳውዲ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆኑት ሙሀመድ ካቢራ የኢትዮጵያ መንግስት 361 የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠታቸውን፣ ሳውዲ በኢትዮጵያ ታላቁ ኢንቨስተር መሆኑን ገልጸዋል። ዶ/ር ቴዎድሮስ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጥሩ ስሜት ላይ እንዳልሆኑ ምንጮች ገልጸዋል። ሚኒሰትሩ በፌስቡክ ላይ ባሰፈሩት መልእክት ጠ/ሚንስትሩን በማጀብ በማንዴላ ቀብር ላይ ሊገኙ ያልቻሉት በጤና ችግር ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል። ኢህአዴግ በሳውድ አረቢያ ላይ ያሳየው የተለሳለሰ አቋም እየተተቸ ነው። ዶ/ር መረራ ጉዲና ሰሞኑን ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ መንግስት በሳውዲ አረቢያ ላይ የያዘውን ፖሊሲ መተቸታቸው ይታወቃል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድህኖም የሚመራዉ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ከ120 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን አስከፊ በሆነ ሁኔታ እንዲባረሩ ቀሪዎቹም ተመሳሳይ እጣ እንዲገጥማቸው በማድረጉ በኩል ተጠያቂ መሆኑን አንዳንድ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለኢሳት ቴሌቭዥንና ጋዜጣ ገልጸዋል። እነዚሁ ሰራተኞች እንደገለጹት የመንግስት የዲያስፖራ ፖሊሲ በአንቀጽ 5 ላይ “ህጋዊ ወረቀት ለሌላቸው በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሚኒስቴሩ ህጋዊ የመታወቂያ ወረቀት  በመስጠት በችግራቸው ጊዜ ለመድረስና እና በአገሪቱ ልማት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያበረታታል፣ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜም አስፈላጊውን ክትትል፣ ድጋፍና እርዳታ ያደርጋል” የሚል ተደንግጎ ቢገኝም፣ በሪያድ የሚገኘው ኢምባሲም ሆነ በጅዳ የሚገኘው ቆንስላ ለኢትዮጵያውያኑ ህጋዊ ወረቀት በመስጠት አሁን የተከሰተው አደጋ እንዳይከሰት ማድረግ ይችል ነበር።

ለዚህም መንግስት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ነው ሲሉ እነዚሁ ሰራተኞች ገልጸዋል። ከዚህ የበለጠ የከፋ አደጋ አልነበረም የሚሉት ሰራተኞች፣ መስሪያ ቤቱ ያሳየው ተነሳሽነት እና በሁዋላም ከተጠያቂነት ለማምለጥ በሚል ከስደተኞች ጋር ፎቶ ግራፎችን በመነሳት ችግሩን ለማድበስበስ ተሞክሯል ይላሉ። ህጉ የወጣው ለይስሙላ ነው ካልተባለ በስተቀር በዲያስፖራ ፖሊሲ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ለኢትዮጵያውያኑ ህጋዊ ወረቀት በጊዜው በመስጠት ችግሩን ማስቀረት ይቻል ነበር የሚሉት እነዚሁ ሰራተኞች በመካከለኛው ምስራቅ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ችግር ፈጥነው በመድረስ ያሳዩት ተሳትፎ በፖሊሲው ላይ ሳይቀር መገለጹን አውስተዋል።

በአንቀጽ አንድ ተራ ቁጥር 2 ላይ “አብዛኞቹ ሙያ የሌላቸው ወይም በከፊል ሙያ ያላቸው በመካከለኛው ምስራቅ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መንግስትና አገር ጥሪ ባቀረበላቸው ጊዜ በፍጥነት የሚደርሱ፣ በአገራቸው የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሳተፉና ለቤተሰቦቻቸው በየጊዜው ተቆራጭ ገንዘብ የሚልኩ ናቸው” ሲል ይገልጻቸዋል። የአለም ባንክ ኢትዮጵያ በእየአመቱ በውጭ ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ 3 ቢሊዮን 200 ሚሊየን ዶላር እንደምታገኝ የገለጸ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙት በአረብ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች ህጋዊ የመታወቂያ ወረቀት በማደል ችግሩ እንዳይከሰት ለማድረግ ለምን እንዳልቻለ እስካሁን አሳማኝ ማብራሪያ አልሰጠም።

## የደቡብ ሱዳኑ መፈንቅለ መንግስት መክሸፉን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ተናገሩ

በቅርቡ ከሱዳን እራሷን አግልላ የራሷን መንግስት የመሰረተቻዉ አዲሷ አፍሪካዊት አገር ደቡብ ሱዳን የመንግስት ግልበጣ ሙከራን አስመልክቶ በደረሰባት ብጥብጥ ወደ እርስ በርስ ግጭትና እልቂት እያመራች መሆኗ ተገለጸ። የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን እንደዘገቡት በዚህ ሳምንት መጀመሪያ በተነሳው የእርስ በእርስ ግጭት ሳቢያ እስከ አሁን 800 የሚጠጉ ዜጎች ተገድለዋል፤ 20 ሺ የሚሆኑ ዜጎችም በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ጥገኝነት ተይቀዋል። በፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር እና በቀድሞው ምክትላቸው ሪክ ማቻር መካከል የተነሳው ውዝግብ የዲንቃና የኑዌር ጎሳዎችን እርስ በርስ እንዲዋጉ እያደረጋቸው መምጣቱን ዘገባዎች ያመለከቱ ሲሆን ወደከፋ የእርስ በእርስ እልቂት ሊያመራ እንደሚችልም ስጋታቸውን እየገለጹ ነው። የሳልቫ ኪር አመራር ሪክ ማቻርን መፈንቅለ መንግስት ለማደረግ አሲረዋል በሚል የከሰሰ ሲሆን የውስጥ ምንጮች እንዳብራሩት ግን በሃገሪቱ የተንሰራፋው ሙስና እና ዘረኛ አስተዳደር ለግጭቱ መንስኤ መሆኑን ነው። የሃገሪቱ ጦር በዚህ ምክንያት ለሁለት የተከፈለ ሲሆን የሪክ ማቻር ደጋፊዎች ጆንግሌ አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎችን ተቆጣጥረዋል፤ በሌሎች አገሪቱ ክፍሎችም ውጊያዎች እየተካሄዱ ነው። ከስልጣን የተባረሩት ሪካ ማቻር ፕሬዚዳንት ሳል ቫኪር ስልጣን እንዲለቁ ጠይቀዋል።

የአዲሲቷ አገር መሪ የሆኑት ሳልቫኪር  የቀድሞው ምክትል ፕሬዚዳንት ሪክ ማቻር ታማኝ ወታደሮች መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሌሊቱን ተኩስ መጀመራቸውን ተናግረዋል። ችግሩ በቁጥጥር ስር መዋሉን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ እንዲህ አይነቱን ድርጊት እንደማይታገሱትና ሙከራውን ባደረጉት ላይ ሁሉ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስዱ ተናግረዋል። የአገሪቱ ቴሌቪዥን ከጠፋ ከሰአታት በሁዋላ እንደገና ስራ ጀምሯል። እስካሁን ድረስ ምን ያክል ሰዎች እንደሞቱ አልታወቀም። በደቡብ ሱዳን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለኢሳት እንደገለጹት 1 ኢትዮጵያዊ በተኩሱ ልውውጥ ተገድሏል። በደቡብ ሱዳን ከ50 ሺ ያላነሱ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ይነገራል።

አንዳንድ ታዛቢዎች ግጭቱ ሊቀጥል ይችላል ይላሉ። በዲንቃና ንዌር ጎሳዎች መካከል ያለው የቆየ ፉክክር ለአሁኑ ግጭት መነሳት ምክንያተ ነው ተብሎአል። ፕሬዚዳንቱ ከዲንቃ ሲሆኑ፣ ምክትላቸው የነበሩት ደግሞ ንዌር ናቸው። ፕ/ት ሳልቫኪር የራሳቸውን ጎሳ አባላት ወደ ስልጣን በማምጣት ሀይላቸውን እያጠናከሩ የሚል ትችት በተቃዋሚዎቻቸው ይቀርብባቸዋል።

የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር ተሞክሮ የነበረው መፈንቅለ መንግስት መክሸፉን ቢናገሩም ግጭቱና እልቂቱ ዘሬም ድረስ እንዳልበረደ ረዩተርስ ዘግቧል። አልፎ አልፎ ይሰማ የነበረው ተኩስ በተከታታይ መሰማቱን የገለጸው ረዩተርስ፣ የአሜሪካ ልዩ ልኡክ የሆኑት ዶናልድ ቡዝ ሁኔታው ውጥረት የበዛበትና ያልተረጋጋ መሆኑን ገልጸዋል።እስካሁን ባለው መረጃ 26 ሰዎች እንደተገደሉ ቢታወቅም አንዳንድ የመገናኛ ብዙሀን ከ60 በላይ ወታደሮች እንደተገደሉ እየዘቡ ነው። ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር የቀድሞው ምክትላቸው ስልጣን ለመያዝ ሲሉ የጀመሩት አመጽ ነው ይላሉ።በርካታ ዜጎች በየኢምባሲዎች ተጠልለው እንደሚገኙ ታውቋል። በአገሪቱ የሚገኙ ከ50 ሺ ያላነሱ ኢትዮጵያውያንን እጣ ፋንታ በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግስት እስካሁን ያለው ነገር የለም።

## አያሌዉ ጎበዜ ከስልጣኑ ተባረረ

ኢትዮጵያ ዉስጥ የብሄር ብሄረሰቦች ጭቆና አበቃ፤ ከዛሬ ጀምሮ ብሄር ብሄረሰቦች እራሳቸዉን በራሳቸዉ ያስተዳድአሉ ሲል የነበረዉ ወያኔ የአማራዉን ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አያሌው ጎበዜን ከስልጣን ከስልጣን አባርሮ ሌላ የወያኔ አገልጋይና አሻንጉሊት የሆነ ግልሰብ በቦታዉ ማስቀመጡን ዘጋቢዎቻችን  ከባህር ዳር በላኩልን ዜና ገለጹ። የአያሌዉ ጎበዜን ከስልጣን መነሳት አስመልክቶ በደረሰን ዜና መሰረት ግለሰቡ ከስልጣን የተነሳዉ የተነሳው የአማራ ክልል ምክር ቤት በፌዴራል መንግስት ትዕዛዝ አስቸኳይ ስብሰባ ካደረገ በኋላ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ከዚሁ ጋር አብሮ የደረሰን ዜና እንደሚያሰረዳዉ የአያለዉ ጎበዜ የሚቀጥለዉ ሚና በአምባሳደርነት ወደ ዉጭ አገር መሄድ ሊሆን ይችላል የሚል ከፍተኛ እምነት አለ። አያሌዉ ጎበዜ በአምባሳደርነት የታጨዉ ከፖለቲካው ገለል ለማድረግ መሆኑን ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

እንደ ምንጮቻችን መረጃ ከኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለሱዳን የተሸጠው መሬትን የማካለል ጉዳይ ጋር በተያያዘ የአያሌው ጎበዜ ያለአግባብ ከስልጣን መነሳት ምክንያት የክልሉ ምክርቤት አባላት ውስጥ ከፍተኛ ክፍፍል ወያኔ በአሻንጉሊትነት ያስቀመጠው ሃይለማሪያመ ደሳለኝ በቅርቡ ሱዳን ሄዶ የወያኔ አገዛዝ ለሱዳን የሸጠውን መሬት ለማካለል ተስማምቶ መመለሱ የሚታወስ ነው። በጠባብ የጎሰኛ አስተሳሰብ የሚመራው የወያኔ አገዛዝ አከብረዋለሁ የሚለውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ምክንያት በማድረግ በጅጅጋ ከተማ ታቆሽሻላችሁ ተብለው ከታሰሩት ዜጎች መካከል ከ40 በላይ ሰዎች መሞታቸው ታወቀ።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz
በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።   g7radio@ginbot7.org

## ለሚቀጥሉት ሶስት አመታት ለመንግስት ሰራተኛው የሚጨመር ደሞዝ አይኖርም ተባለ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በየቀኑ እያደገ የሚሄደዉ የዕቃዎች ዋጋ በፈጠረዉ የኑሮ ዉድነት የመንግስት ሰራተኞች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቁ ቢሆንም በሚቀጥሉት ሶስትና አራት አመታት የመንግስት ሰራተኞችን አስመልክቶ ምንም አይነት የደሞዝ ጭማሪ እንደማይደረግ ሁለት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች ተናገሩ። እንደ ባለስልጣኖቹ አባባል የመንግስት ሰራተኞቹ ምንም ያክል ችግር ቢደርስባቸዉም ወይም የዋጋ ግሸበቱ እያደገ ሄዶ የመግዛት አቅማቸዉን ቢያሟሟዉም በመንግስት በኩል ምንም የሚደረግ ነገር አለመኖሩን ያመለክታል።

የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ሳሚያ ዘካርያ እንደተናገሩት የፍጆታ እቃዎች የዋጋ ግሺበት በአንዴ የሚለካው ለአምስት አመታት ነው። ያነጋገርናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በየቀኑ በሚጨምረው ገበያ እና በምርት እጦት እየተማረሩ መሆኑን ይገልጻሉ።የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባጠናው ጥናት 57 በመቶ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ ገቢውን የሚያውለው  ለምግብ  ነክ ጉዳዩች ነው። አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት እንዴት ያዩታል ተብለው የተጠይቁት ወ/ሮ ሳምያ “የዋጋ ግሸበቱን አይተው የደሞዝ ማሰተካከያ የሚያደርጉ ሃገራት አሉ፤ ማስተካከያ ካልተደረገ የዋጋ ግሺበቱን ጫና መቀነሳ አይቻልም” የሚሉት ወ/ሮ ሳምያ  ማሰተካካያ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም የመንግስት ፖሊሲ እንደማይፈቅድ ተናግረዋል። “አሁን ያለውን የኑሮ ውደነት እኔም አውቃለሁ” የሚሉት ሃላፊዋ፣  ችግሩን ስር እንደሰደደ የምረዳው በርካታ ሰራተኞች ከአዲስ አበባ ለመልቀቅ ማመልከቻ ለማስገባት ሲረባረቡ ሳይ ነው” ብለዋል።

“የወር ደሞዛቸው  የቤት ኪራይ መሸፈን እንኳን አለመቻሉ የሚናገሩት ወ/ሮ ሳምያ፣ የህዝብና ቤት ቆጠራ ስናይ አሁን ከዚህ ቤት ሰው ይኖራል ወይ ብለን እንጠይቃለን” በማለት በኢትዮጵያ ስላለው የኑሮ ውድነት በግልጽ ተናግረዋል።የፋይናንስ ና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አብርሃም ተከስተ “የመንግስት ሰራተኛው በልቶ የማደር ፈተና ውስጥ እና መጠለያ ቤት እጦት እንደሚያንገላታው እናውቃለን” ያሉ ሲሆን፣   ጫናው በርካታ ባለሙያዋች ስራቸውን እንዲለቁ እንዳደረጋቸው መረጃ አለኝ ብለውል። “በ2006 ዓ.ም ምንም አይነት የደሞዝ ጭማሪ በጀት የለም” ያሉት ሚኒስትር ዲኤታው፣ እንዲያውም የፋይናንስ እጥረት እያጋጠመ በመምጣቱ ከቴሌ ኮሚኒኬሺን ፣ ከመብራ ሃይል እና ከውሃ ከሚሰበሰበው በብድር መልክ ተቀብለን ያስተላለፍነው የደሞዝ ክፍያ በርካታ ነው ሲሉ ለዘጋቢያችን ተናግረዋል። የደሞዝ ጭማሪው ለመጭዎች ሶስት እና አራት አመታት የሚታይ ጭማሪ ሊኖረው አይችልም ሲሊ ሚኒስትር ዴኤታው ለዘጋቢያችን በስልክ አረጋግጠዋል።

## ጅጅጋ ዉስት ከተማ ታቆሸሻላችሁ ተብለው ከታሰሩት ሰዎች ከ40 በላይ መሞታቸዉ ተሰማ

ወያኔ 9ኛውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ጅጅጋ ዉስጥ ለማክበር ሽር ጉድ በሚልበት ወቅት የከተማዋን ንጽህና ታቆሸሻላችሁ ተብለዉ  ታፍሰዉ  ከጅጅጋ 25 ኪሜ ገደማ ወደምትገኘዉ ቀብሪበያህ ከተማ እስር ቤት እንዲገቡ ከተደረጉት መካከል ከ40 በላይ ሰዎች ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ በመሞታቸውንና በታሰሩበት አካባቢ እንዲቀበሩ መደረጉን ከጂጂጋ የደረሰን ዜና አስረዳ።  ከሟች ጓደኞቻቸዉ ጋር ታስረዉ በህይወት የተረፉት አንዳንዶቹ ከታሰሩበት ተልቅቀዉ ወደፈለጉበት ቦታ እንዲሄዱ የተደረገ ሲሆን  ብዙዎቹ የጎዳና ላይ ተዳዳሪዎች በመሆናቸዉ መሄጃ እንደሌላቸዉ ታዉቋል።

“ከተማ ታቆሸሻላችሁ እና ለጸጥታ ስጋት ትሆናላችሁ” በሚል ምክንያት ታስረው ከነበሩት ሰዎች መካከል ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በጋሪ መግፋት እና በጉልበት ስራ የሚተዳደሩ ነዋሪዎች፣ አይነ-ስውሮች፣ አካለ ስንኩላን፣  መታወቂያ አሳዩ ሲባሉ የክልሉን መታወቂያ ማሳየት ያልቻሉ፣ ከተለያዩ አካባቢዎች በመምጣታቸው ጸጉረ ልውጥ ተብለው የተያዙ የሌላ በጅጅጋ መታወቂያ ለማውጣት 1 መቶ 15 ብር የሚጠይቅ ሲሆን፣ በችግር ምክንያት መታወቂያ ያላወጡና በድንገት መታወቂያ በተጠየቁበት ጊዜ ማሳየት ያልቻሉ በርካታ ሰዎች በእስር ቤት ውስጥ እንዲያሳልፉ ተደርገዋል።

የክልሉን የጸጥታ ዘርፍ ሃለፊ የሆኑትን አቶ አብዱላሂ ኢትዮጵያን ለማግኘት በተደጋጋሚ ስልክ ብንደውልላቸውም ልናገኛቸው አልቻልንም።በአገር ውስጥ ያሉ ወይም በውጭ የሚኖሩ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች፣ ጋዜጠኞች ወይም የቀይ መስቀል ሰራተኞች ሰዎቹ የተቀበሩበትን ቦታ ቦታው ድረስ ሄደው  በማየት  መረጃውን ይፋ እንዲያደርጉ  ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ሰዎች ጠይቀዋል። አካባቢው  የመከላከያ ሰራዊት አባላት በብዛት የሚንቀሳቀሱበት በመሆኑ ያለክልሉ ፈቃድ ፎቶግራፎችን ማንሳት አይቻልም። መንግስት የብሄር ብሄረሰቦች በአሉ የለምንም የጸጥታ ችግር ማለፋን ቢገልጽም፣ በጸጥታ እና በገጽታ ግንባታ ስም ዜጎች ለከፍተኛ ስቃይ መዳረጋቸውን የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ። በጅጅጋ የተካሄደውን ዝግጅት በአብዛኛው ከህወሀት ጋር ዝምድና ያላቸው ሰዎች እንዳዘጋጁ ኢሳት መዘገቡ ይታወቃል። ከውስኪ አቅርቦት እስከ በዛር ዝግጅት፣ ከማስታወቂያ ስራ እስከ እቃ አቅርቦት በአብዛኛው የህወሀትና ከህወሀት ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች እንዳዘጋጁትና በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አግኝተውበታል።

## ዋ ማዲባ ዋ ማንዴላ

ዋ ማንዴላ!
ዋ ማዲባ!
ይቺን ፀሐይ ማን ነገረህ
ከጨለማ ውስጥ በቅለህ
ከድጥ ወደ ማጥ ብትዳክር
ብርሃን በልብህ አሳድረህ
"እንካቹ!" ብትል ብትጮህ
ሰሚ ተነፍጎህ
አንድ ቀን እንደሚነጋ
በደልና ግፍ ማክተሚያ እንዳለው ስትዘክር፤

ለተጨቆነ እንዲበራ
ቃል ተጋብተህ እስከትሞት እንደምትዳክር።

ንገረኝ ማዲባ
ጥርኽልኝ ማንዴላ
ማን ነገረህ እንዲህ እንዲነጋ?
ግዙፉን ያፓርታይድ ዱላ
ሳትሰለች ቅንጣት ሳትፈራ

ቢወርድብህ
በወጣት ዘመን ቢቸክህ፤
እግርህ በግረሙቅ ታብቶ
እኩል ዕድሜህን ቀምቶ
በግዞት ቢጠበጥብህ

የልብህ ብርሃን በራ እንጅ
መቸ ተረታህ ለፈረንጅ።
ይቺን ቀን ፀሐይ እንድትፈካ ለጭቁኖቹ
እንድትበራ ማን ሹክ ብሎህ ይሆን ምስራቹን?
ዋ ማዲባ!
ዋ ማንዴላ!
የሰባዊነት ትሩጁማኑን ባንታየን

ቢተቹህ ቢንቁህ
ሰላማዊ ትግልህን ቢያንጓጉጡህ
የልብህን ብርሃን መቸ አወቁ?

ትግልህ አፋፍ ላይ ደርሶ
ሰላም ለህዝብህ አንግሶ
ሥልጣን በጅህ ሲገባ

ያቺን የልጅነትህን ብርሃን
በመካያው ላለም ብታሰፍን፤

ጥቁር የሰላም ፀር ይመስል
ዓለም በራድ ቆዝሞ -

በደም መቃባት በበቀል
ዛሬ- ነገ ፈነዳ ብሎ -

በሰቅቀን ተብሰክስኮ
ጉድ ለማየት ሲያደባ
ተቃቅፈህ ጸናህ ከዴክለርክ፤
ሰላም መስፈኑን አበሰርክ።

ዋ ማንዴላ!
ዋ ማዲባ!
እንዴት ይሆን
የገባህ ፍቅር
እንዴት ይሆን
የገባህ መላ
ዋ /ን/ ማን ማንዴላ!!!

እነንቶኔ
አንሰው አንሰው
ከዘር ወርደው
ብሔር ከጎሣ ሰፍረው
ሰፍረው
ቁ-ል-ቁ-ል
ደ-ቅ-ቀ-ው
ተ-በ-ጣ-ጥ-ሰ-ው
በሥልጡን ዘመን
ፊት ገ-ጥ-ጠ-ው
ገዢ ነን ብለው
ካገር ከህዝብ ተስፈንጥረው
እንደማይጠግብ መጋዣ -

የህዝቤን ደም መ-ጥ-ጠ-ው፡
መ'ጠው፡
አሳፈሩን በመሪ ስም ስናያቸው፡
ማይችሉት መንበር ላይ ሲንቧቸሩ
ብናያቸው።

አንተ ግና
የበቀል ፍሬ እንዳይረባ
ባስደናቂ ፍቅር አስተጋባህ፤

ዋ ማንዴላ! ዋ ማዲባ!
የሰላም የፍቅር ሐውልት
የጥቁር ብልህ ተምሳሌት ፡፡

----------//------------

ዘምንሊክ ከሲድኒ